ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን ግንቦት 27 2000 ዓ.ም

---

## ህዝብ በረሃብና በበሽታ ያልቃል፤ የሃገሩ ገዥዎች ግን ህዝብን ለመሰለል ከፍተኛ የሃገር ሃብት ያወድማሉ።

ህዝብ የሚገለገልባቸውን የኢንተርኔት እና የሞባይል አገልግሎቶች ለመቆጣጠር እና በወያኔ የስለላ መረብ ወስጥ ለማስገባት፣ ወያኔ የዘመኑን የኤሌክትሮኒክ የስለላ መሳሪያዎችንና ኤክስፐርቶችን በመግዛት ከፍተኛ ወጪ ማድርጉን፣ የተለያዩ የሚድያ አውታሮች ቀደም ብለው መዘገባቸውን በማስታወስ፤ ይህ የወያኔ የስለላ ፕሮጄክት፣ የስለላውን መሳሪያ መጠቀም የሚችሉ በርካታ ወጣቶችን በማሰልጠን በሙሉ ሃይሉ የሚንቀሳቀስበት ምእራፍ ላይ መድረሱን የግንቦት7 ዜና ዘጋቢ አስታውቋል።

የግንቦት7 የዜና ምንጭ አያይዞ እንደገለጸውም በአዲስ አበባ፣ አይቤክስ ከሚባለው የቴሌ የማሰልጣኛ ጣቢያ፣ ከተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ወደ 3 ሽህ የሚጠጉ ወጣቶች የተለየ ስልጠና የተሰጣቸውና አሁንም እየተሰጣቸው ነው። በእዚህ ማእከል ውስጥ ስልጠናውን ከሚሰጡት የውጭ ዜጎች በተጨማሪ፣ በኤሌክትሮኒክ የግንኙነት ዘዴዎች ላይ ከፍተኛ እውቀት ያላቸው፣ ለአገዛዙ በከፍተኛ ብር በመገዛት በእዚህ እኩይ ተግባር ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያንም እንዳሉ የግንቦት7 የዜና አቅራቢ መረዳት ችሏል። የእነዚህ ዜጎች ማንነት በጥንቃቄ ከተጣራ በኋላ ስማቸው ለግንቦት7 እንደሚተላለፍ የተናገሩ ሃገር ወዳድ ተባባሪዎች ማግኘቱንና ይህ መረጃ እንደደረሰው ለተበዳዩ ህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ሪፖርተራችን አስታውቋል።

በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያላችው እነዚሁ ወጣቶች የቴሌኮምኒኬሽን ባለሙያተኛ በሚል ስም የስለላ ሥራውን የጀመሩ ሲሆን፣ ሌሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ደግሞ ስልጠናውን ጨርሰው ስራ ባይጀምሩም ከቴሌ መስሪያ ቤት ደሞዝ እየተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል። ከአንዳንዶቹ ወጣቶች በተገኘው መረጃ መሰረት፣ ያለምንም ስራ፣ ደሞዝ እየተከፈላቸው እንዲቆዩ የተደረጉት፣ ለእዚህ ስለላ ስራ ታማኝ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለማጣራት ወያኔ/ኢህአዴግ የጀመረውን የስለላ ስራ እስኪጨርስ ድርስ እንደሆነ ይናገራሉ።

በሌላ በኩል የወያኔ/ኢህአዴግ ጠቅላይ ሚንስቴር፣ ከፍተኛ ባለስልጣናትና የጸጥታ ሹሞች ብቻ የሚጠቀሙበት ቪስታ (VISTA) የሚባል ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት መሆኑን የግንቦት 7 ሪፖርተር ገልጾ፣ ይህም አገልግሎት በቀጥታ ሱልልታ ከሚገኘው የሳተላይት ጣቢያ ጋር  የተገናኘ መሆኑን አስረድቷል። እንደ ግንቦት 7 የዜና ምንጭ፣ ባለሥልጣኖቹ የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎቶችን የሚያገኙት VPN ( virtual private network) በሚባል የግል ኔትወርክ አማካይነት  ሲሆን፣  የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎቶች ለህዝብ በተዘጉበት ጊዚያት ገዥዎቹና የፀጥታ ሹሞቹ እንደፈለጉ የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። በሃገሪቱ ውስጥ በኢንተርኔት አገልገሎት መስጠት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ለንግድ ስራቸው የሚያስፈልጋቸው የግል፣ የትምህርትና የስልጠና ተቋማትና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የኢንተርኔት ግልጋሎት፣ የወያኔ/ኢህአዴግ ገዥዎች እንዳሻቸው እንደ ቧንቧ ውሃ መዘጋትና መክፈት የቻሉበት ሁኔታ የመጣው ለራሳቸው ብቻ የሚጠቀሙበት የኢንተርኔትና የሞባይል አገልግሎት ስላላቸው መሆኑ ታውቋል። ገዥዎቹ ስልጣናቸውን ለመንከባከብ ሲሉ በየግዜው በሚዘጉት የኢንተርኔትና የሞባይል አገልግሎት የተነሳ፣ በሃገር ኢኮኖሚና በህዝብ ላይ የሚደርሰው

መንገላታት ደንታ የማይሰጣቸው መሆኑን በየግዜው ግልጋሎቱን እንዲዘጉ ትእዛዝ ከሚሰጣቸው ባለሙያተኞች የግንቦት7 ዜና አቅራቢ መረዳት ችሏል፡፡

ከዚህም በተጫማሪ መለስም ሆነ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖቹ የሚጠቁሙባቸው የሞባይል ስልክ አይነቶች (G8 ) የተባሉ ሲሆኑ፣ እነዚህ አይነቶቹ ስልኮች የተለያዩ የኔትወርክ አገልግሎቶችን በቀላሉ መጠቀም የሚያስችሉ ናቸው ተብሏል፡፡

በአሁኑ ግዜ የሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ባዶ በሆነበት፣ አመታዊ የአገዛዙ በጀት ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ እጥረት ባሳየበት ወቅት፣ ህዝብ በረሃብ መርገፍ በጀመረበት፣ የኑሮ ውድነት ሃገሬውን ባሳበደበት አስከፊ የመከራ ዘመን፣ አሁንም የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ለስለላ መሳሪያና ለስለላ ስራ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪና በጀት መድቦ በተጠናከረ መንገድ መንቀሳቀስ መቀጠሉን ለስለላው ስራ ቅርበት ያላቸው ሃገር ወዳዶች ለግንቦት 7 ዜና አስታውቀዋል፡፡ ከእዚህም ጋር በማያያዝ ወያኔ የደረሰበትን የባጀትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለማሟላት የአለም ባንክን፣ የአለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅትና የምእራብን መንግስታት ብድርና ምጽዋት እንዲሰጡት የልመና ፌስታሉን ይዞ በሚዞርበት ወቅት፣ ይህ አገዛዝ ምን ያህል ሃብት ህዝብን ለመሰለልና ለማፈን እያባከነ እንደሆነ፣ የወጣቶቹን የቴሌ ስልጠና እና ሌሎቹንም የአፈና መዋቅሮቹን ወጪዎች በመጥቀስ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሊያጋልጡት፣ አገዛዙ የሚጠይቀውን የገንዘብ እርዳታ የሰብአዊ መብት ጥሰትንና የዴሞክራሲ መብቶች ረገጣ ሳያቆም እንዳይሰጠው የተለመደውን እንቅስቃሴያቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው የሚል ጥሪ ሪፖርተራችን ካነጋገራቸው ዜጎች ማግኘቱን አስታውቋል፡፡

በሃገራችን ተከታታይ ገዥዎች ህዝብን በስለላና በጉልበት አፍነው ለመግዛት ያደረጉት ሙከራ ያልተሳካ፤ ሁሉም ተዋርደው ከስልጣን እንደተባረሩ ሁሉ ወያኔ/ኢህአዴግም በህዘብ እንዲህ በተተፋበት ሁኔታ የፈለገውን የስለላና የአፈና አቅም ቢያጠናክር መጨረሻው ከቀድሞዎቹ አገዛዞች የተለየ እንደማይሆን፣ የወያኔን የስለላ ድርጊት ዝርዝር የሰሙ የእድሜ ባለጸጋ አረጋዊ ለግንቦት7 ዜና ገልጸዋል፡፡ ይህ የአረጋዊው ትንበያ በቅርቡ እውን ይሆናል የሚል እምነት የአብዛኛው የሃገሪቱ ዜጋ እምነት እየሆነ መምጣቱን ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙ በማተት ዘጋቢያችን ዜናውን አጠናቋል፡፡